# የሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን

“ሠርቶ አደሩ ሕዝብ...በሕገ መንግሥቱ ዝግጅት ቀጥተኛ ንቁና ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ማድረጉ እጅግ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን የትግሉ ውጤቶች ዋናውና መብቱ ነው”

ጓድ መንግሥቱ ኃ/ማርያም
ነሐሴ 1977

ECLN

በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ረቂቅ ሕገ መንግሥት ላይ ከሕዝብ በተገኙ አስተያየቶች ላይ በመመሥረት የተደረጉ ማሻሻያዎች

ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያን እንመሠርታለን !

# በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ረቂቅ ሕገ መንግሥት ላይ ከሕዝብ በተገኙ አስተያየቶች ላይ በመመሥረት የተደረጉ ማሻሻያዎች

ነሐሴ 27/1978

ECLN

# መግቢያ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ረቂቅ ሕገ መንግሥት በሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን ተዘጋጅቶ በኢሠፓ ማእከላዊ ኮሚቴ ውሳኔ መሠረት ለሕዝብ ውይይት እንዲቀርብ መደረጉ ይታወሳል ::

ረቂቁ ለሕዝብ ውይይት መቅረብ የሚችል ስለመሆኑ የኢሠፓ ማእከላዊ ኮሚቴ ውሳኔ ካስረፈበት በኋላ ለተለያዩ መድረኮች ቀርቦ ሰፊ ውይይት ተካሂዶበታል፤ ጠቃሚ የማሻሻያ አስተያየቶችም ተሰጥተውበታል ::

ውይይት ከተካሄደባቸውና አስተያየት ከተሰጠባቸው መድረኮች ዋና ዋናዎቹ:-

- በአገር አቀፍ፣ በክፍለ ሀገርና በወረዳ ደረጃ ለመሪ ካድሬዎች የተዘጋጁ ሴሚናሮች፣
- የኢሠፓ መሠረታዊ ድርጅቶች፣
- የኢትዮጵያ ሕዝብ የተወያየባቸው መሠረታዊ የመወያያ መድረኮች፣
- የአብዮታዊው ጦር አባላት የተወያዩባቸው መሠረታዊ የመወያያ መድረኮች፣
- ለሕዝባዊ ድርጅቶች አገር አቀፍ የአመራር አካሎች የተዘጋጁ የመወያያ መድረኮች፣
- በውጭ አገር ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን የተዘጋጁ የመወያያ መድረኮች፣

ናቸው ::

በነዚህ መድረኮች ሁሉ ከፍተኛ የፖለቲካ ግምት የማሰጠው ተሳትፎ ታይቷል :: በውይይቱ ሂደትም የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ የረቂቁ ሕገ መንግሥቱን ይዘት እንዲረዳው ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፣ አጥጋቢ ውጤትም ተገኝቷል ::

በተጠቀሱት መድረኮች በተካሄደው ውይይት እጅግ ብዙ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ቀርበዋል ። የተነሱት ጥያቄዎችና አስተያየቶች ሁሉም ከአሁን ቀደም ያልታዩና አዳዲስ ናቸው ባይባልም ለተወያዩ ሕዝብ አመለካከት ተገቢውን ግምት በመስጠት ረቂቁን የማዳበሩ ተግባር ከውይይቱ ዓላማዎች አንዱ እንደመሆኑ ይህንኑ በመሠረትነት በመያዝ ተገቢውን ማሻሻያ ለማድረግ እንዲቻል ከላይ ከተጠቀሱት መድረኮች የተገኙ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ሁሉ በመለክ በመለካቸው ተደራጅተው ተመርምረዋል ።

በውይይቱ የተገኙት ጥያቄዎችና አስተያየቶች ሲጠቃለሉ፡—

— ፖሊሲን የሚመለከቱ፣

— ቴክኒካል የሆኑ፣

— ገንዘብን የሚመለከቱ፣

ጉዳዮች ሆነው ተገኝተዋል ።

በነዚህ ላይ በመመሥረትና የረቂቅ ሕገ መንግሥቱን የቋንቋ ጥራት ለመጠበቅ በተከናወነው ተግባር በሚከተሉት የረቂቅ ሕገ መንግሥቱ አንቀጾች ላይ ማሻሻያዎች ተደርገዋል /የፊደላትና የነጥብ ማስተካከያዎች እንዲሁም ለውጥ ያልተደረገባቸው አንቀጾች በዚህ ላይ አልተጠቀሱም/ ።

1. <u>መቅድም</u>

- የመጀመሪያው ፓራግራፍ "እና" በሚል እንዲጀምር ሆኖ እንደሚከተለው ይነበብ:-

  "<u>እና</u> የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ <u>አሁን ከምንገኝበት</u> ኋላ ቀርነት ወደ ከፍተኛ የእድገት ደረጃ ለመሸጋገር የዘመናት አኩሪ ታሪካችንን መሠረት በማድረግ ፍትሕ፣ እኩልነትና ማኅበራዊ ብልጽግና የሰፈነበት ሶሻሊስት ኅብረተሰብ ለመገንባት በከፍተኛ አብዮታዊ ትግል ላይ <u>እንገኛለን</u>::"

- አራተኛው ፓራግራፍ ላይ "አገናጽፏታል" ከሚለው ቀጥሎ የሚከተለው ገብቶ ይነበብ:-

  "በአርበኞቿ የአምስቱ ዓመታት ትግልና መስዋዕትነትም ፋሺዝምን ድል በመምታት በታሪክ ተረጋግጦ የቆየውን የነፃነት አርማዋን ከማውለብለቧ የሚገታት ኃይል አለመኖሩን እንደገና አስመስክራለች::"

- ከስድስተኛው ፓራግራፍ ላይ "በምርት" የሚለው ቃል ወጥቶ እንደሚከተለው ይነበብ:-

  "በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ በዚህ የረጅም ዘመን ታሪኩ በልዩ ልዩ ማኅበረ ኢኮኖሚ ሥርዓቶች ውስጥ የተጓዘ ሲሆን በዚሁ ሂደት ላይ መራራ የመደብ ጭቆናና የበዝባዥ ጊዜ አሳልፏል:: በተለይም በፊውዳሉ ሥርዓት ውስጥ የነበረው ግንኙነት ገበሬውን አስከፊ በሆነ የጭቆና ቀንበር ሥር ጥሎት እንደነበር ይታወቃል:: ፊውዳሎችም በየጊዜው በመካከላቸው በሚያነሱት ግጭትና ጦርነትም ሕዝቡ ሲማገድ፣ የጉልበቱ ውጤት የሆነውን ምርት በልዩ ልዩ መንገድ ሲቀማ፣ ረሃብ፣ በሽታና እልቂት ሲፈራረቅበት ኖሯል::"

- ስምንተኛው ፓራግራፍ "አብዮቱ አነሳሱ ላይ" ይል የነበረው "አብዮቱ በተቀጣጠለበት ወቅት" በሚለው ተተክቶ፣ "አመራር" ከሚለው ቀጥሎ "ሰጭ አካል" የሚለው ገብቶ፣"...

.../

ECLN

በማስወገድ" ይል የነበረው" ... በማስወገድና በተከታታይ" በሚለው ተተክቶ፣ "... በማከታተልም..." ይል የነበረው" "...በመውሰድ..." በሚል ተተክቶ፣ "... ጥሏል ::" ይል የነበረው " ጣለ ::" በሚል ተተክቶ፣ "... ተደርገዋል ::" ይል የነበረው"...ሆነዋል" በሚለው ተተክቶና " ... እንዲቀዳጅ ተደርጓል :: "ይል የነበረው" ... ሊቀዳጅ ችሏል ::" በሚለው ተተክቶ እንደሚከተለው ይነበብ:—

" አብዮቱ በተቀጣጠለበት ወቅት የተደራጀ ግንባር ቀደም አመራር ሰጪ አካል ስላልነበረ የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ወገን የሆነው የመለዮ ለባሹ ክፍል ትግሉን አስተባብሮ መምራት ጀመረ :: ከዚያም የዘውዱ አገዛዝን በማስወገድና በተከታታይ ልዩ ልዩ አብዮታዊ እርምጃዎችን በመውሰድ ለአዲስ ሕዝባዊ ሥርዓት መሠረት ጣለ :: የገጠር መሬት፣ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶች፣ ታላላቅ የማምረቻ፣ የማከፋፈያና አገልግሎት ሰጭ ተቋሞች የሕዝብ ሀብት ሆነዋል :: ለብሔረሰብ፣ ለጾታና ለሃይማኖት እኩልነት ሁኔታዎች ተመቻችተዋል :: ሠርቶ አደሩ ሕዝብ በየፈርጁ እየተደራጀ በአገሩ ጉዳይ ወሳኝ የሚሆንበት መብት ሊቀዳጅ ችሏል ::"

— ዘጠነኛው ፓራግራፍ "እኛ" በሚል እንዲጀምር ሆኖ ዘጠነኛው፣ አሥረኛውና አሥራ አንደኛው ፓራግራፍ እንደሚከተለው ይነበቡ:—

"እኛ የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ ፍትሕ፣ እኩልነትና ብልጽግና የሰፈነበትን የአዲሱን ኅብረተሰብ ግንባታ ትግል በውል ለመያያዝ የበቃነው በቀላሉ አይደለም :: የመደብ ጠላቶቻችን ከፊታችን የደቀኗቸውን ብርቱ ፈተናዎች መወጣት ቀዳሚ ተግባራችን ነበር :: ቀድሞም ለነፃነታችንና ለአንድነታችን መከበር ስንዋደቅ እንደኖርን ሁሉ፣ ዛሬ ደግሞ " አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት" ብለን በመነሣት ለዓላማችን ገብ መምታት እየተፋለምን አሁን ለምንገኝበት ለፈጣን ማኅበራዊ እድገት አመቺ ወቅት ለንበቃ ችለናል ::

.../

ECLN

በአሁኑ ጊዜ <u>እና</u> የኢትዮጵያ ሠርቶ አደር ሕዝብ ዋና ትኩረታችን ልማት <u>ሲሆን</u>፣ በአጠቃላይ ዓላማችንም ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን <u>እያጠናቀቅን</u> ለሶሻሊዝም ግንባታ ተፈላጊውን ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረት መጣል ነው :: ይሁን እንጂ ፀረ አብዮትና ፀረ ሶሻሊዝም የሆኑ <u>ኢምፔሪያሊስትና የአድኅሮት</u> ኃይሎች ጠቀና የእድገት <u>ጉዟችንን</u> ለማደናቀፍ ከመሞከር <u>ስለማይታቀቡ</u> ይህን አድራጎታቸውን መቋቋም ሌላው የትግላችን ግንባር ነው ::

<u>እና የኢትዮጵያ</u> ሠርቶ አደር ሕዝብ የመራራ ትግላችን ውጤት የሆነውን የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲን አመራር የተቀዳጀን በመሆኑ፣ የፖለቲካ ባህላችንን እያዳበርን ዓላማችንን ከግብ ለማድረስ በምንችልበት አስተማማኝ ሁኔታ ላይ እንገኛለን :: በዚህ መሠረት የአባቶቻችን አደራ ከማስከበር <u>ጋር</u> የአዲስ ሥርዓተ ማኅበር ግንባታን ታሪካዊ ተግባር በስፋት ተያይዘናል :: ጥረታችን ፍሬ እያስገኘ <u>ለግባችን</u> መብቃት እንችል ዘንድ የአዲሱ ፖለቲካ ሥርዓት መሟላት አስፈላጊ ሁኔታ ነው ::

— በ12ኛው ፓራግራፍ " መሠረታዊ መብቶችና ግዴታዎች የሚከበሩበትን፣ " የሚለው " መሠረታዊ ነፃነቶችና መብቶች የሚጠበቁበትንና ግዴታዎች የሚከበሩበትን፣ " በሚለው ተተክቶ ይነበብ።

2. <u>አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 1</u>

— " በዕደ ጥበብ ሙያተኛውና " ይል የነበረው " በዕደ ጥበብ ባለሙያውና " በሚለው ተተክቶ እንደሚከተለው ይነበብ፣

" የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በሠራተኛውና በገበሬው ኅብረት፣ በምሁሩ፣ በአብዮታዊ ሠራዊት፣ <u>በዕደ ጥበብ ባለሙያውና</u> በሌሎች ዲሞክራሲያዊ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ የሠርቶ አደሩ ሕዝብ መንግሥት ነው :: "



ECLN

3. አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2

— "ያራምዳል" ይል የነበረው "ያጠናክራል" በሚለው ተተክቶ እንደሚከተለው ይነበብ:—

"የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የብሔረሰቦችን እኩልነት ያስከብራል፤ ትምክህተኝነትንና ጠባብነትን ይዋጋል፤ የሁሉንም ብሔረሰቦች ሠርቶ አደሮች አንድነት ያጠናክራል ::"

4. አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 3

— "በመስጠት" ይል የነበረው "በማድረግ" በሚለው ተተክቶ እንደሚከተለው ይነበብ:—

"የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በተለይ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ለሚገኙት ትኩረት በማድረግ የብሔረሰቦችን ያልተመጣጠነ የኢኮኖሚ እድገት ደረጃ በደረጃ በማስተካከል የጋራ ብልጽግናቸውን ያረጋግጣል ::"

5. አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2

— "የሥልጣን አካላቱ" ይል የነበረው "የመንግሥት ሥልጣን አካላት" በሚለው፣ "መፈጸም አለባቸው" ይል የነበረው "ተፈጻሚ ይሆናሉ" በሚለው ተተክቶ እንደሚከተለው ይነበብ:—

"ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ የሚገኙ የመንግሥት ሥልጣን አካላት በምርጫ ይቋቋማሉ :: የመንግሥት ሥልጣን አካላት ማእከላዊ አመራርንና የአካባቢ ሐሳብ አመንጭነትን በተግባር ያውላሉ :: የበላይ አካላት ውሳኔዎች በበታች አካላት ተፈጻሚ ይሆናሉ :: የበታች አካላት ለበላይ አካላት ተጠሪ ናቸው ::"

6. አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1

— "በግንባር ቀደምትነት የሚታገል" ይል የነበረው "የቆመ ግንባር ቀደም" በሚል ተተክቶ እንደሚከተለው ይነበብ:—

.../

ECLN

11. <u>አንቀጽ 17</u>

— "... ሊገዛ" ከሚለው ቀጥሎ " ተገቢውን ክፍያ በማድረግ" የሚል ሐረግ ገብቶ እንደሚከተለው ይነበብ:—

" መንግሥት ለሕብረተሰቡ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በሕግ በሚወሰነው መሠረት ማንኛውንም ንብረት ሊገዛ፣ <u>ተገቢውን ክፍያ በማድረግ</u> ሊገለገልበት ወይም ካሣ በመክፈል ሊወርስ ይችላል ::"

12. <u>አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 3</u>

— " የኅብረተሰቡ" ከሚለው ቀጥሎ " ሥራ ወዳድነት" የሚለው ገብቶ እንደሚከተለው ይነበብ:—

"መንግሥት የኅብረተሰቡ <u>ሥራ ወዳድነት</u>፣ የሥራ ችሎታና ፈጠራ እንዲዳብር ያደርጋል ::"

13. <u>ስለ ስፖርት — አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 2</u>

— ስፖርትን በሚመለከት በረቂቅ ሕገ መንግሥት የሚከተለው ተጨማሪ ንዑስ አንቀጽ ገብቷል:—

" <u>መንግሥትና ኅብረተሰብ ዜጎች የአካል ማሰልጠንና ስፖርትን እንዲያዘወትሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል ::</u>"

14. <u>አንቀጽ 22</u>

— "... ለሆኑትም" ከሚለው ቀጥሎ ያለው" ለቤተሰቦቻቸው" የሚለው ወጥቶ በምትኩ " ታጋዮች ቤተሰቦች" የሚለው ገብቶ እንደሚከተለው ይነበብ:—

" የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ሲያስከብሩና አብዮቱን ሲጠብቁ ጉዳት ለደረሰባቸው ታጋዮችና መስዋዕት ለሆኑትም <u>ታጋዮች ቤተሰቦች</u> መንግሥትና ኅብረተሰብ ልዩ እንክብካቤ ያደርጋሉ ::"

.../

ECLN

15. <u>አንቀጽ 23</u>

— "መንግሥት" ከሚለው ቀጥሎ "ኅብረተሰብ" የሚለው ገብቶ
እንደሚከተለው ይነበብ:—

"መንግሥትና <u>ኅብረተሰብ</u> የባህልና የታሪክ ቅርሶች
እንዲጠበቁ፣ ጎጂ ልማዶች እንዲወገዱ፣ ሠርቶ
አደሩ ሕዝብ በሶሻሊስት ሥነ ምግባር እንዲታነጽና
ወዛደራዊ ባህል ደረጃ በደረጃ እንዲሰፍን ያደርጋሉ ::"

16. <u>አንቀጽ 30</u>

— "ሳለው" እና "ዕድገት" የሚሉት ወጥተው እንደሚከተለው
ይነበብ:—

"የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የማይገ
ሰሰው የአገሮች ብሔራዊ ሉዓላዊነትንና የግዛት አንድ
ነትን፣ አንዱ በሌላው የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አለመግባ
ትን፣ አለመግባባቶችን በሰላም መፍታትን እና በአጠቃላ
ይም የገለልተኝነት መርሖችን መሠረት በማድረግ ለሕዝቦች
መደጋገፍ፣ ለጋራ ልማትና ከጎረቤት አገሮች ጋር በመል
ካም ጉርብትና ላይ ለተመሠረተ ግንኙነት መጠናከር ጥረት
ያደርጋል ::"

17. <u>አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ 1</u>

— "ሴቶች ከወንዶች ጋር" ይል የነበረው "ሴቶችና ወን
ዶች" በሚለው ተተክቶ እንደሚከተለው ይነበብ:—

"በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሴቶችና
ወንዶች እኩል መብት አላቸው ::"

18. <u>አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 1</u>

— "በጋብቻ ላይ ጋብቻ የተከለከለ ነው ::" የሚለው ወጥቶ
እንደሚከተለው ይነበብ:—

"ጋብቻ ለአካለ መጠን በደረሱ በአንድ ሴትና በአንድ
ወንድ መካከል በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነው ::
ባልና ሚስት በቤተሰብ ግንኙነታቸው እኩል መብት
አላቸው :: ጋብቻ የመንግሥት ጥበቃ ይደረግለታል ::"

.../

ECLN

19. አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 1

- " ካልተያዘ" የሚለው " ካልተገኘ" በሚለው፣ " በቁጥጥር ሥር አይውልም" የሚለው " አይያዝም" በሚለው ተተክቶ እንደሚከተለው ይነበብ:-

" ማንኛውም ሰው ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተገኘ ወይም በዐቃቤ ሕግ ትእዛዝ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ ካልሆነ ወይም ሕግ ከሚደነግገው በስተቀር አይያዝም ::"

20. አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 2

- " በቁጥጥር ሥር የዋለ" የሚለው " ማንኛውም የተያዘ" በሚለው ተተክቶ፣ " . . . የሚያስፈልገውን" ከሚለው ቀጥሎ " ጊዜ" የሚለው ቃል ገብቶ እንደሚከተለው ይነበብ:-

" ማንኛውም የተያዘ ሰው በ48 ሰዓት ውስጥ ወደ ፍርድ ቤት መቅረብ አለበት፤ ሆኖም ይህ ጊዜ ወደ አቅራቢያው ፍርድ ቤት ለመድረስ የሚያስፈልገውን ጊዜ አይጨምርም ::"

21. አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 3

- " በከፍተኛ" የሚለው " በከባድ" በሚለው ተተክቶ፣ " ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል" የሚለው ወጥቶ፣ " ሰው" ከሚለው ቀጥሎ " በሕግ በሚወሰነው መሠረት" የሚለው ገብቶ እንደሚከተለው ይነበብ:-

" ማንኛውም ተከሳሽ ራሱ የመከላከል ወይም የሕግ ጠበቃ የማቆም መብት አለው :: በከባድ ወንጀል ተከሶ የሕግ ጠበቃ ለማቆም አለመቻሉ ለተረጋገጠለት ሰው በሕግ በሚወሰነው መሠረት መንግሥት በነፃ ያቆምለታል ::"

22. አንቀጽ 59

- " አጠባበቅ" ይል የነበረው " አከባበር" በሚለው ተተክቶ እንደሚከተለው ይነበብ:-

.../

" የዜጎች ነፃነቶችና መብቶች አጠቃቀምና የግዴታዎች <u>አከባበር</u> በሕግ ይወሰናል :: የዜጎች ነፃነቶችና መብቶች አጠቃቀም በሕግ ገደብ የሚደረግበት የመንግሥትና የኅብረተሰብ ጥቅም፣ እንዲሁም የሌሎች ግለሰቦች ነፃነቶችና መብቶች እንዲከበሩ ብቻ ነው :: "

23. <u>አንቀጽ 68</u>

— " መካከል " የሚለው ወጥቶ እንደሚከተለው ይነበብ:—

" ብሔራዊ ሸንጎ በዓመት አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል :: አስቸኳይ ስብሰባ በመንግሥት ምክር ቤት ወይም በሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት ውሳኔ ወይም ከአባላቱ ከሦስት አንዱ እጅ ሲጠይቅ ይጠራል :: "

24. <u>አንቀጽ 69 ንዑስ አንቀጽ 2</u>

— " የቀደመው " የሚለው " የነባሩ " በሚለው ተተክቶ እንደሚከተለው ይነበብ:—

" የሸንጎው የሥራ ዘመን ከመፈጸሙ ሁለት ወር በፊት የአዲሱ ሸንጎ ጠቅላላ ምርጫ ይከናወናል :: <u>የነባሩ</u> ሸንጎ የሥራ ዘመን እንደተፈጸመ ያለው የመንግሥት ምክር ቤት አዲሱን ሸንጎ ይጠራል :: "

25. <u>አንቀጽ 69 ንዑስ አንቀጽ 3</u>

— " ብሔራዊ " የሚለው ወጥቶ እንደሚከተለው ይነበብ:—

" አዲሱ ሸንጎ እንደተሰበሰበ የመጀመሪያ ተግባሩ በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 64 ንዑስ አንቀጽ 4 የተመለከቱትን የመንግሥት አካላት አባላት መምረጥ ይሆናል :: "

26. <u>አንቀጽ 69 ንዑስ አንቀጽ 4</u>

— "ብሔራዊ" የሚለው ወጥቶ እንደሚከተለው ይነበብ:-

" አዲስ የተመረጠው ሸንጎ ተሰብስቦ የመንግሥት ምክር ቤትንና የሪፐብሊኩን ፕሬዚዳንት እስከሚመርጥበት ጊዜ ድረስ ያለው የመንግሥት ምክር ቤትና ያለው ፕሬዚዳንት በሥልጣን ላይ ይቆያሉ ።"

27. <u>አንቀጽ 71</u>

— "ይኖሩታል" የሚለው በ"ያቋቁማል" ተተክቶ እንደሚከተለው ይነበብ:-

" ብሔራዊ ሸንጎ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚሽኖችን ያቋቁማል ።"

28. <u>አንቀጽ 72</u>

— "ፕሬዚዳንት" እና "ኮሚሽኖች" ከሚሉት ቀጥሎ "ብሔራዊ" የሚለው ገብቶ፣ እና "በአገር አቀፍ አካሎቿቸው አማካይነት ሕዝባዊ ድርጅቶች" የሚለው "የራስ ገዝ አካባቢ ሸንጎዎች" ከሚለው ቀጥሎ እንዲገባ ሆኖ እንደሚከተለው ይነበብ:-

" የመንግሥት ምክር ቤት፣ የሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት፣ <u>የብሔራዊ</u> ሸንጎ ኮሚሽኖች፣ <u>የብሔራዊ</u> ሸንጎ አባላት፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፣ ከፍተኛና የአስተዳደር አካባቢና የራስ ገዝ አካባቢ ሸንጎዎች <u>እና በአገር አቀፍ አካሎቿቸው አማካይነት ሕዝባዊ ድርጅቶች</u> ሕግን የማመንጨት መብት አላቸው ።

29. <u>አንቀጽ 73 ንዑስ አንቀጽ 1</u>

— "መካከል" የሚለው ወጥቶ እንደሚከተለው ይነበብ:-

" ብሔራዊ ሸንጎ ከአባላቱ ከሦስት ሁለት እጅ ሲገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይኖረዋል ።"

30. <u>አንቀጽ 75</u>

— "የብሔራዊ" የሚለው ገብቶ እንደሚከተለው ይነበብ:—

" <u>የብሔራዊ</u> ሸንጎ አባላት የሠርቶ አደሩ ሕዝብ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴዎች ናቸው::"

31. <u>አንቀጽ 76 ንዑስ አንቀጽ 1</u>

— "ካልተያዘ" ይል የነበረው "ካልተገኘ" በሚለው፣ "በቁጥጥር ሥር አይውልም" ይል የነበረው "አይያዝም" በሚለው ተተክቶና "ያለ" ከሚለው ቀጥሎ "ብሔራዊ" የሚ ለው ገብቶ እንደሚከተለው ይነበብ:—

" አንድ የሕዝብ እንደራሴ ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ <u>ካልተገኘ</u> በስተቀር ያለ <u>ብሔራዊ</u> ሸንጎ ወይም ሸንጎው ባልተሰበሰበበት ጊዜ ያለ መንግሥት ምክር ቤት ፈቃድ <u>አይያዝም</u>፣ በወንጀልም አይከሰስም::"

32. <u>አንቀጽ 80</u>

— "ለመቆም" የሚለው "አንድነት" ከሚለው ቀጥሎ ገብቶ፣ "እንደዚሁም" የሚለው ወጥቶ፣ "ለመቆምና ለተፈጻሚነታቸው" የሚለው "ተፈጻሚነት" በሚለው ተተክቶ እንደሚከተለው ይነበብ:—

" አንድ የሕዝብ እንደራሴ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት የሚከተለውን ቃል ይገባል:—

ለኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ነፃነትና አንድነት <u>ለመቆም</u>፣ ለሶሻሊዝም ታማኝ ለመሆን፣ የሠርቶ አደሩን ሕዝብ ፍላጐትና ጥቅም ለማስቀደም፣ ለዚህ ሕገ መንግሥትና ለሌሎቹም ሕጐች <u>ተፈጻሚነት</u> ለመሥራት ቃል እገባለሁ::"

.../

33. <u>አንቀጽ 88 ንዑስ አንቀጽ 2</u>

– " የሚወሰዱ አርምጃዎች" የሚለው " መሠረት የሚደረጉ ውሳኔዎች" በሚለው ተተክቶ እንደሚከተለው ይነበብ:–

" በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 <u>መሠረት የሚደረጉ ውሳኔዎች</u> በፕሬዚዳንት ልዩ ድንጋጌ የሚታወጁ ሆነው ለሚቀጥለው የብሔራዊ ሸንጎ ስብሰባ ቀርበው መጽደቅ ይኖርባቸዋል ::"

34. <u>አንቀጽ 93 ንዑስ አንቀጽ 5</u>

– " ዕድገት" የሚለው ወጥቶ እንደሚከተለው ይነበብ:–

" የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ዕቅዶችን ያዘጋጃል፤ ለብሔራዊ ሸንጎ ያቀርባል፤ ሲጸድቁም ተግባራዊነታቸውን ያረጋግጣል፤"

35. <u>አንቀጽ 93 ንዑስ አንቀጽ 7</u>

– " ... ግንኙነት" ከሚለው ቀጥሎ" ለብሔራዊ ሸንጎ፣ ለመንግሥት ምክር ቤትና" የሚለው ገብቶ፣ እንዲሁም " ... ያቀርባል" ከሚለው ቀጥሎ " ተግባራዊነቱንም ያረጋግጣል" የሚለው ገብቶ እንደሚከተለው ይነበብ:–

" ስለሪፐብሊኩ የውጭ ግንኙነት <u>ለብሔራዊ ሸንጎ</u>፣ <u>ለመንግሥት ምክር ቤትና</u> ለሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት ሃሣብ ያቀርባል፤ <u>ተግባራዊነቱንም ያረጋግጣል</u>፤

36. <u>አንቀጽ 93 ንዑስ አንቀጽ 12</u>

– " በየወቅቱ" የሚለው " ፕሬዚዳንት" ከሚለው ቀጥሎ ገብቶ እንደሚከተለው ይነበብ:–

" ስለሥራው እንቅስቃሴ ለብሔራዊ ሸንጎና ሸንጎው በማይሰበሰበበት ጊዜ ለመንግሥት ምክር ቤትና ለሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት <u>በየወቅቱ ዘገባ</u> ያቀርባል ::"

.../

ECLN

37. <u>አንቀጽ 98 ንዑስ አንቀጽ 6</u>

– " ቋሚ" የሚለው ወጥቶ እንደሚከተለው ይነበብ:–

" ከአባላቱ መካከል የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይመርጣል፤ ሥራውንም ይቆጣጠራል፤"

38. <u>አንቀጽ 99 ንዑስ አንቀጽ 5</u>

– " ዕድገት" የሚለው ወጥቶ እንደሚከተለው ይነበብ:–

" የአካባቢውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕቅዶችና በጀት ያዘጋጃል፤ ከጸደቀም በኋላ በሥራ ላይ ያውላል፤

39. <u>አንቀጽ 99 ንዑስ አንቀጽ 7</u>

– " በየወቅቱ" የሚለው " አካል" ከሚለው ቀጥሎ እንዲገባ ሆኖ እንደሚከተለው ይነበብ:–

" ለአካባቢው ሸንጎ ለበላይ አስፈጻሚ አካል <u>በየወቅቱ</u> ዘገባ ያቀርባል :: "

ECLN

40. <u>አንቀጽ 102 ንዑስ አንቀጽ 1</u>

– " የሌሎች" የሚለው " የአካባቢ" በሚለው ተተክቶ እንደሚከተለው ይነበብ:–

" የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች የሚመረጡት በብሔራዊ ሸንጎ ነው፣ የአካባቢ ፍርድ ቤቶች ዳኞች በየአካባቢያቸው ሸንጎዎች ይመረጣሉ :: "

41. <u>አንቀጽ 106</u>

– " ማንኛውም ሰው" የሚለው ወጥቶ " ባለጉዳይ" በሚለው ቃል ተተክቶ እንደሚከተለው ይነበብ:–

" ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ተግባራቸውን የሚያከናውኑበትን ቋንቋ ለማይችል <u>ባለጉዳይ</u> የትርጉም አገልግሎት ይሰጣሉ :: "

42. <u>አንቀጽ 109 ንዑስ አንቀጽ 1</u>

- " እንደዚሁም " የሚለው " ና " በሚለው፣ " የማረጋገጥ ሥልጣን የዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ነው ። " ይል የነበረው " የዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ያረጋግጣል ። " በሚለው ተተ ክቶ እንደሚከተለው ይነበብ፡-

  " የመንግሥት አካላት፣ ሕዝባዊ ድርጅቶች፣ ሌሎች ማኅበራት፣ ባለሥልጣኖቻቸውና ማንኛውም ግለሰብ ሕግን ማክበራቸውንና የሕጉንም አንድ ወጥ አፈጻጸም የዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ያረጋግጣል ። "

ECLN